# የሶስት ምርጫዎች ወግ (ክፍል ሶስት)

ዮናስ 03-06-15

የመድበለ ፓርቲ ስርአትን መነሻ አድርጎ ማጠቃለያ ላይ የደረሰው ወጋችን መቋጫው ሚዲያ ይሆናል፤ የሚዲያ ጉዳይ ሃሳብን በነፃ ከመግለፅና ከመናገር ነፃነት (freedom of expression) ጋር የማይነጣጠልና አንዱ ያለአንዱ ህልውና የሌለው መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተለይ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሃገራት ይቅርና አድገዋል ለሚባሉትም ጨምር ሚዲያ ያለው ሁለንተናዊ አስተዋፅኦ ቀላል የማይባል መሆኑም ይታወቃል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ በአንድ ሃገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ላይ እንዳለው አስተዋፅኦ በሥርዓት ካልተመራና በህግ አግባብ ካልተያዘ የነበረውን እንዳልነበር ከማድረግ ጀምሮ ሃገርን የማተራመስ አቅሙም ከፍተኛ እንደሆነ በተለያዩ ሃገራት ያለፉና ከሚዲያ ጋር የተያያዙ ስኬቶችንና መበላሸቶችን ማስታወስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አምባገነናዊ የሆኑቱ ደግሞ ሚዲያውን ለሀገር ልማት ካለው ፋይዳ ይልቁን ከስልጣናቸው አኳያ በመመዘን ጭርሱኑ የሚገድቡበት ስለመሆኑም አንድ ሁለት ሃገራትን ዞር ዞር ብሎ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በዘመነ ደርግ የነበረው የሃገራችንም የሚዲያ ትዝታ ይኸው ነው፡፡ ሀሳብን በነፃ የመግለፅም ሆነ የመናገር ነፃነትን ከመገደቡም በላይ የትኛውም አይነት (ለመንግስት ፋይዳም) እንኳ ቢሆን ያለ ቅድመ ምርመራ ለህትመት የማይበቃ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በዘመነ ኢህአዴግ ያስተዋልነው ሚዲያን የተመለከተ ጉዳይ ደግሞ የተለየ ነው፡፡ መለየቱ ደግሞ አስቀድሞም የሚጠበቅ ነው፡፡ አስቀድሞ የመጠበቁ ምክንያትም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ስለዚሁ ሃሳብን በነጻ የመግለፅ መብትን ዋና ማዕቀፍ ላደረገው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ታግለዋልና ነው፡፡

ቅድማ-ምርመራ ላይመለስ ከመቀበሩም ባሻገር ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መበትም ሆነ የመናገር ነፃነት ህገመንግስታዊ እውቅናም አግኝተዋል፡፡ ከህገመንግስታችን 106 አናቅፆች 2/3ኛ የሚሆነውም፣ ሀሳብን በነፃ ከመግለፅ መብት ጋር የተያያዙቱ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን የተመለከተ የሆነውም ሥርዓቱ አስቀድሞም የታገለለትና የሞተለት በመሆኑ መሆኑንም መገመት አይከብድም፡፡ ያም ሆኖ ግን በግል ፕሬሱና ፕሬሱን ከላይ በተመለከተው አግባብ በፈጠረው መንግስት መካከል በተለይ ባለፉት 10 አመታት እሰጣ ገባው እየከረረና ከመስመር እየወጣ መሆኑም ተስተውሏል፡፡ በእርግጥ የሚበዙት ስለዴሞክራሲያዊ መብቶች ከልብ የቆሙ ዜጎችና ተቋማት ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› እያሉ የጮኹባቸውን ጊዜያቶች ብናስታውስም ለፕሬሱ ፈቃድ ከመስጠት ጀምሮ የሚቆጣጠረው አካል የረዘመ ጊዜን በትዕግስት ማሳለፉ ይታወቃል፡፡ አንዳንዶቹም ስለምን ተብሎ በህመንግስት ጉዳይ ላይ የረዘመ ቀርቶ ቅፅበታዊ ትዕግስት ያስፈልጋል? የሚሉ ጥያቄዎች ቢያቀርቡም ዴሞክራሲያችን ታዳጊ መሆኑን ከግምት በመከተትና ከዛሬ ነገ እንደሚሻሻሉ በመገመት፤ በእናቱም አንባቢው ህብረተሰብ አንቅሮ ሊተፋቸው እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ መሆኑ ቢገለፅም አሁን ላይ ግን ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል››ጊዜው አልፏልና እርምጃው መታየት ጀመረ፡፡

በምርጫ 2007 ዋዜማ ሚዲያውን በተመለከተ አቢይ የነበረው ዜናም ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድና የትርምስ አቅጣጫ በመንደፍ የተሰማሩ የፕሬስ ውጤቶች ላይ መንግስት ክስ መመስረቱን የተመለከተው እና ክሱን ተከትሎ ከፕሬሱ

በኩል ሲሰጥ የነበረው ግብረ መልስ መሆኑ ይታወሳል፡፡ ይህውም ከፕሬሱ እና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲሁም ከውጭ አለምአቀፍ አንዳንድ ተቋማት ይወርድ የነበረው ውግዘት ነው፡፡ በመሰረቱ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት በማናቸውም ሁኔታና አግባብ ያሻውን መናገርም ሆነ መፃፍ የሚያስችል መብት ስለመሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 29 የተመለከተ ቢሆንም ገደብ ሊደረግባቸው የሚገቡ እና እኒህም ያለአንዳች ወዘተርፈ በግልፅ ተለይተው በዚያው አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 ስር የተመለከቱ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እነዚህን የማይደፈሩ እና የማይገሰሱ ገደቦች መጣሳቸው በራሱ የፅንፈኛነታቸውን ጥግ የሚያሳይ ቢሆንም፤ ሌሎችም የበሬ ወለደ ዘገባዎቻቸውና ትርክቶቻቸው ፍፁም ከጋዜጠኝነት መርሆም ጋር ሆነ እንደ አክቲቪስትም ከአክቲቪስቲዝም መርሆዎች ጋር በሚላተሙና ፍፁም መርህ አልባ በሆኑ መንገዶች ላይ የሚገኙ የፕሬስ እና የተቃውሞ ስብስቦች ስለመሆናቸው በርካታ አስረጅዎች ሊያውም  ተከሳሽ የነበሩ መፅሄቶችን ወደ ኋላ መለስ ብለን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አንድ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ መሆኑና አለመሆኑ ከሚገለጽባቸው  ጉዳዮች አንዱ ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃ የሚገልፁበት መብት ሲጎናፀፉ መሆኑም ላይ ልዩነት ያለው አካል አይኖርም፡፡ ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃ ለመግለፅ ከሚጠቀሙባው መንገዶች ወይም ዘዴዎች ዋነኛው ደግሞ ሚዲያ ነው፡፡ MC Quail የተባሉ ተመራማሪ ባቀረቡት ጥናት እንዳመለከቱት ነፃ ፕሬስ ማለት ቅድመ ምርመራ የሌለበትና ሚዲያው መረጃ እንዳያሰራጭ የሚከለክል የመንግስት ህግ የሌለበት እንዲሁም ሚዲያው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነፃነት ኖሮት አገልግሎት ለሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች ጥቅም ሲባል መረጃ የማግኘት መብት ያለው ማለት ነው፡፡ Rovert የተባለ ፀሃፍት በበኩሉ 1994 ላይ ጉዳዩን በተመለከተ ይፋ ባደረገው ጥናት የፕሬስ ነፃነት ማለት መንግስታዊ ቅድመ ምርመራ ሳይኖር የመናገር፣ ብሮድካስት የማድረግና የማተም መብት ሲሆን መብቱ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ለሚፈጠሩ የህግ ጥሰቶች ህጋዊ ተጠያቂነትን የያዘ ነው ይላል፡፡

ነፃ ሚዲያ የሚለውን ሃልዮት በተመለከተ ጥናት ካደረጉት ምሁራን መካከል Rozumilowicz (20020 ያቀረበው ጥናት ይገኛል፡፡ ጥናቱ እንዳመለከተው ከሆነ *ነፃ ሚዲያ የሚኖረው ከሞኖፖሊ ነፃ ሆኖ ከማንኛውም ቡድን ወይም ሃይል ቁጥጥር ነፃ ሆኖ ለተጠቃሚዎች በእኩልነትና በውጤታማነት ተደራሽ ሆኖ አገልግሎት መስጠት ሲችል ነው፡፡*

እነዚህን መሰረታዊ የነፃ ሚዲያና ፕሬስ እንዲሁም ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት መነሻዎች ይዘን  ወደፍትህ ሚንስቴር ክስ ስናመራ  እነዚህ በጽንፈኝነት ጠርዝ ላይ የሚገኙ ፕሬሶች "ነፃው ፕሬስ ወይም ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በኢትዮጵያ አልተከበረም፤ ተደፍጥጧል” በሚል ሊሞግቱ ቢሞክሩም አስረጂዎቻችን የሚያረጋግጡት ግን "ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በማይቀለበስ ደረጃ መረጋገጡንና ይኸውም ህገመንግስታዊ ዋስትናም የተደረገለት መሆኑን  ይልቁንም ለክስ የበቁት የግል ፕሬሶች ነፃ ሳይሆኑ  አፋኝ መሆናቸውን ነው፡፡”

በህገመንግስቱ ክፍል ሁለት (አንቀፅ 29 ንኡስ አንቀጽ 6) ስር እደተገለፀው ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ሂደት ውስጥ ገደብ ሊጣልበት የሚገባውን ነገር  በተመለከተ እንደሌሎች ሀገራት የአስተሳሰቡ ውጤት ላይ ሳይሆን የሚያስከትለው አደጋ ላይ መሆኑ ትክክል አይደለም፡፡ በሌሎች ሀገሮች ህገመንግስታት ውስጥ ሀሳብን በነፃነት ከመግለፅ መብት ጋር ተያይዞ የተቀመጡት ገደቦች የአስተሳሰቡ ውጤት ላይ ሲሆን በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ግን  "ግን፤ ነገር ግን፤ ሆኖም፤" የሚሉ የማገጃ ቅጽሎች በማስገባትና በዚሁም መነሻ ተከታታይ ህጎች በማውጣት ስርዓቱ የህጋዊ ህገወጥነትን መንገድ እየተከተለ ነው፡፡" በማለትም

መሚገቻቸውን ትክክል ለማስመሰል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ጥናቱን ለምርጫ 2007 የተሳለ ቢላዋ ነው ሲሉ የሚከሱት እነዚህ የፕሬስ ውጤቶች ምርጫ 2007ን ታሳቢ ያደረገ አጀንዳ በጋራ ቀርፀው እየተንቀሳቀሱና በምርጫ 97 የተሞከረውን የቀለም አብዮት ተከትሎ የታሰሩ ሃይሎችን ጭምር በአዲስ ጋዜጣ ቀላቅለው የተመለሱበትን ተጨባጭ ሃቅ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የሁሉም (የግል ፕሬሶች) አጀንዳ አንድና ተመሳሳይ ነው፡፡ የሃሳብ ብዝሃነት (diversity) የላቸውም፡፡ የአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ ቀጣዩ ምርጫ፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እሮሮ፣ የህዳሴው ግድብ፣ የኑሮ ውድነት፣ የትምህርት ስርዓት፣ ሙስና እና የመሳሰሉትን እንደ ዋነኛ የሃሳብ መዘውር በመያዝ ያለ አንዳች ተጨባጭ መነሻና ያለበቂ መረጃና ማስረጃዎች የአንድ ወገን ማጣቀሻ ወይም የነሂዩማን ራይትስ ዎችንና የአውሮፓ ህብረትን የነተቡ ሪፖርቶች አራግፈው በማጣቀስ፣ ከላይ የተመለከቱትን የሃሳብ መዘወሪያዎች በአሉታዊ መንገድ በመመልከትና መንእሴውም ስርዓቱ እንደሆነ በመሰበክ የትርክታቸውን መውጪያ የቀለም አብዮት በማድረግ የሚጠናቀቁ እንደሆነ የወጋችን ማጠንጠኛ በሆነው 10 አመታት ውስጥ የወጡትን መፅሄቶችና ጋዜጦች በመመልከት ማረጋገጥ ተችሎናል፡፡

መቼም ማንኛውም እና የትኛውም ሚዲያ በማናቸውም የባለቤትነት ይዞታ ስር ሆኖ ሲቋቋም የኤዲቶሪያል ፖሊሲ፣ ፕሮፌሽናል መለኪያ (standard) እና የራሱ ሀሳብ የሚኖረው እንደሆነ (ሊኖረው እንደሚገባ) ግልፅ ነው፡፡

ታዲያ ይህ መርህ ባለበት ሁኔታ ከላይ በጠቀስኩላችሁ ጊዜያት ውስጥ ያየናቸው ሚዲያዎች ሽፋን የሰጧቸውን ሃሳቦች ስትመልከቱ፤ በአንደኛው ሳምንት ሁሉም ስለ 66ቱ አብዮት ሲያወሩ፣ በሚቀጥለውም ሁሉም ስለቀለም አብዮት ሲሰብኩ፣ የመረጃ ሞኖፖሊ አለ ብለው በከሰሱበት ብእራቸው በሃሳብ ሞኖፖሊ ተዘፍቀው ታገኟቸዋላችሁ፡፡ በርዕሳቸውና በስያሜያቸው የተለያዩ ግን አንድ ደራሲ የሚፅፋቸው እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ተመሳሳይ መልእክት ያላቸውን ትርክቶችም በተመሳሳይ ቀን አትመው የነበረ መሆኑንም ይገነዘባሉ (ለዚህ ደግሞ አንድ አይነት ርእሰ አንቀፅ ይዘው እስከመውጣት የደረሱትን *ሰፍሮ ታይምስ* እና *የኛ ፕሬስን* ያስታውሷል)። እነዚህ የፕሬስ ውጤቶች ለጋዜጠኝነት የሙያ መለኪያ መስፈርት (professional standard) እውቅና የማይሰጡ ብቻ ሳይሆን ፍላጎቱም ያላቸው እንዳልሆነ የሚያረጋግጡ ትክርቶቻቸውን መለስ ብሎ በመመልከት ማንነታቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በእርግጥ የትኛውም ሚዲያ የራሱ አቋም ቢኖረውምና እንደሚኖረው ቢታወቅም በጥቃቅን ነገሮችም ላይ የፅንፈኛውን ጥግ ይዘው የሚሰሩ እንደሆነም ተከሳሽ ከሆኑቱ የህትመት ውጤቶች ያረጋግጡ፡፡

እነዚህ ወገኖች፣ ከገቢያቸው ወጪያቸው የሚበልጥ መሆኑንም አንዳይረሱ፤ ጥያቄው *ገበያ ውስጥ የመቆየታቸው (survive) ምስጢር ምንድን ነው?* የሚለው ነው፡፡ ጋዜጣ መቼም ፊቱ ይናገራል፤ የመሸጫ ዋጋውም ከፊት ገፅ ተመልክቷል፤ የማተሚያ ዝቅተኛ ዋጋ ከ12 ብር እንደማያንስ ለጉዳዩ ቅርበት ያለን ሁሉ እናውቃለን፡፡ ታዲያ ወይ እንደነ *ፎርቹን* አልያም እንደነ *ሪፖርተር* በማስታወቂያ ያልታጀቡት እንዚህ ጋዜጣና መፅሄቶች ገበያ ውስጥ የመቆየታቸው መነሻ ቢፈተሽ ምን ሊሆን እንሚችል መገመት ይከብድ ይሆን? አይመስለኝም።

እንደሚታወቀው የፕሬስ ነፃነት አንዱ መገለጫ የፋይናንስ ግኙቱ (financial dependency) ነው፡፡ በፋይናንስ ረገድ የራሱ ነፃነት ያለው ፕሬስ የሃሳብ ነፃነት ይኖረዋል፡፡ ተደጓሚ ከሆነ ደግሞ ስለሃሳብ ነፃነትና ስለሃሳብ ብዝሃነት ምንም አይነት ቦታ

አይኖረውም፤ ይልቁንም የገንዘብ ደጓሚውን ሀሳብ እንዲያንፀባርቅ ይገደዳል፡፡ በ10 አመታት ቅኝታችን የተመለከቱት እና ታፍነናል ሲሉ የሚጮሁት የፕሬስ ውጤቶች በተመሳሳይ ቀን ተመሳሳይ አጀንዳ የመለፈፋቸውም ታላቅ ሚስጥርም ይኸው ነው፡፡

በዴሞክራያዊ ስርዓት ውስጥ እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መርሆች ለፕሬሶቹም ሆነ ለማንኛውም ሰው ለፈለገው እና ለመረጠው ሀሳብ እድል የሚሰጥ ቢሆንም በየትኛውም ሃገርና በየትኛውም ሁኔታ በመሰረታዊነት ብሄራዊ ጥቅም የሚባል ነገር እንዳለ እሙን ነው፡፡ የኛዎቹ እና ታፍነናል ሲሉ አፋኝ ሆነው የተገኙቱ ብሄራዊ ጥቅም የሚባል ነገር የማያውቁ ስለመሆናቸው ከህዳሴው ግድብ የ3ኛ ዓመት ክብረ በአል ይልቅ የ1966ቱ አብዮት ቀርቧቸው መገኘቱ ጥሩ ማረጋገጫና የገመናቸውን ጥልቀት የሚያመላክት ነው፡፡  እነዚህ ፕሬሶች የሀሳብ ብዝሃነትን የማይቀበሉ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከእነርሱ የተለየ አቋም የሚያንፀባርቁትን ብቻ ሳይሆን ከዚያም ከዚህም ያልሆኑትን ሚዛናዊ ፕሬሶች እንዲጠፉ አዘውትረው መፃፋቸውም በነፃ ፕሬስ ስም አፋኝ ፕሬስ መሆናቸውን የሚያረጋግጥልን ሃቅ ነው፤ ስርጭቱም የአፋኝነታቸው ሌላኛው ማረጋገጫ ነው፡፡ የግል ሚዲያ ውስጥ አሳታሚ ሆነው እንደገና በአከፋፋይነት ጨዋታ ውስጥ ተሰልፈው መገኘታቸውም እንደዛው፡፡

እንኳንስ በምርጫ አሸንፎ ስልጣንን የያዘ መንግስትን ይቅርና በአባቶች ብሂል እንቧይ ተወርውሮ እስኪመለስ ባለው ቅፅበት ውስጥም ሰልጣኑን የያዘ አካል ዝቅተኛ የሆነው   የቅቡልነት መገለጫ  በስሙ መጠራት ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ለወጋችን ማሳያ በመሆን የተቃኙትና በፕሬስ ተሚጋችነት ስም የቆሙ የእነርሱ ሰፈርተኞች ከ1997 በኋላ ቢያንስ እና ሙያዊም ሆነ የዜግነት ግዴታቸው የሆነውን የኢፌዲሪ መንግስት በስሙ መጥራት ማቆማቸው እሙን ነው፡፡ ከፈለጋችሁ ተመልከቷቸው በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ሆነው ስለ ጸረ ዴሞክራሲ እንደሚዘምሩ፣ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ተከብሮም እንዲከበር እንሰራለን እያሉ ትንሹን የህግ ግዴታ መወጣት ተስኗቸው መንግስትን ‹‹ወያኔ›› በማለት ጽፈው ታገኟቸዋላችሁ፡፡

አንድ የሆነው መልእክታቸው አብዮት አብዮት፣ ለውጥ ለውጥ የሚል መሆኑንም አይተን አምነናልና አይተው ይመኑ ፡፡ ይህ ሰፈር ሚዛናዊ (balance) ሆኖ እየሰራ እና ጥልቅ መርማሪ (critical) ሆኖ እየደገፈና እየተቸ እንዲሁም መፍትሄ እያመነጨ ሳይሆን ያለውንም ወደኋላ እየጎተተና የዱሮውን ሥርዓት እየናፈቀ መሆኑንም ከወጋችን ፍተሻ ማረጋገጥ ችለናል፡፡ ስለሆነም ለብዝሃነት ጥብቅና የቆመውን ስርዓት ለመገርሰስ የተሰለፈውን ፅንፈኛ ሀይል ወግኖ እየሰራ ነው ብንል ከላይ በተመለከቱትና ቀጥሎም በሚመጡት አስረጅዎች ተደግፈን እንጂ ካድሬ ሆነን እንዳልሆነ  የኑፋቄው መንገደኞች እንዲያረጋግጡልን እንሻለን።

ነጻ ነን እያሉ ከገበያ አክራሪ ሃይሎች ጋር የሚነግዱትን በሙያዊ አይን የፈተሹ አንዳንድ ምሁራን ክስ የተመሰረተባቸውን ፕሬሶች ሲጀመር የሀሳብ ብዙሃነትን (The diversity of opinion) ሰለማያሟሉ ለእነርሱ በራሪ ወረቀቶች (phanmplet) እንደሆኑ ያወጉና በዚህም መነሻ ነጻ አውጪም ወቃሽም ለመሆን እንዳልቻሉ በሚገባ አስቀምጠውታል፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው ያሉትን ከላይ የተመለከቱ መከራከሪያዎች የሚዲያውንና የተቃዋሚውን የአብሮነት መነሻ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ መሆኑ ቢገባንም አለመሆን የሚቻልበት እድል መኖሩንም ልንሸፍንላቸው እንደማይገባ ግን ሁሉም ወገን ሊያውቅልን ይገባል፡፡

ከሰማንያ በላይ የሚሆኑ ፓርቲዎች ባሉበት ሀገር ላይ፣ እንደ አሸን ፈልተው እንደ አሸን የሚጻፉ ፕሬሶች ባሉበት ሀገር ላይ፤ ይልቁኑም ምርጫ በደረሰ ቁጥር እየበዙ የሚመጡ ፓርቲዎችና (አላማቸው ምንም ይሁን ምን) ፕሬሶች ባሉበት ሀገር ላይ

የመደራጀትና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት የለም ብሎ መከራከር የጸሀይ መውጫ በምዕራብ ነው ብሎ ሙግት እንደመግጠም ይሆናል፡፡ የግል ቴሌቭዥን አለመስፋፋቱን መነሻ አድርጎ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ተደፍጥጧል ማለትም አመክንዮአዊ አይደለም፡፡

በዓመት ከአምስት ያላነሰ ማስታወቂያ የሚያወጡ ጋዜጣና መጽሄቶች ውድ በሆነው የግብጽ ሻማል ሼክ የመዝናኛ ስፍራ ድረስ ሄደው የሚዝናኑ አሳታሚዎች ስለመኖራቸው የሀገሪቱ የፋይናንሻል ዳታ በመመልከት በኢትዮጵያ የሚዲያ ነጻነት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠ፣ ህገመንገስታዊ እርካብ የጨበጠ፤ ለአፈጻጸሙም አስተማማኝ የሆኑ ተቋማት ተገንብተው መሰረታዊ መደላድል የያዘ ነጻነት መሆኑን፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ይህን ነጻነት ወደፊትም ሊቀለበስ በማይችልበት ደረጃ ላይ ለማድረስ እለት በእለት በአድማስና በጥልቀት እሰፋ የመጣና ልንጠብቀው የሚገባ መሆኑን ካለመቀበል በዚህ ነጻነት ላይ ሙግት መግጠም ሊሆን የሚችለው እውነትን የመሸምጠጥ እንደሆነ አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባውና ለ10 አመታቱ ወጋችን መጠነኛ ቅኝት ካደረግንባቸው ፕሬሶች የተገነዘብነው ሃቅ ነው፡፡

ሰው ግራ ቀኙን ተመልክቶ የያዘውን ሃሳብ ለማዳበርና የሚሻውን ለመቃረም የማይችልበት እንዲሁም በአፈና ውስጥም ሆኖ ያጎለበተውን ሃሳብ ከሌሎች ጋር ለመጋራት እና ለማስተላለፍ የማይችልበት የአፈና ሥርዓት መወገዱን መካድም እውነትን መሸምጠጥ ነው፡፡ የፕሬስ ነጻትን በተመለከተ ህገመንግስታዊ ሙግት የሚገጥሙ ሃይሎች በመሰረታዊነት ሊገነዘቡት የሚገባው ጉዳይ ነጻነቱ ስለፕሬስ ተብሎ ሳይሆን መሰረታዊ ከሆኑ ሶስት ገጽታዎች መሆኑን ነው፡፡ ማንም ለማንም በፈቃዱ ሳይፈልግ የሚከለክለውና ሲፈልግ የሚቸረው እንዳልሆነ የሚያመለክተው የመጀመሪያው ገጽታ ነው፡፡ መረጃ የመስጠት፣ የመቀበልና ፈልጎ የማግኘትን የተመለከተው ደግሞ ሁለተኛው ገጽታ ሲሆን ይህን መረጃ ሃሳብና አመለካከትን ማስተላለፍ ደግሞ ሶስተኛው ገጽታ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ነጻነት ለፕሬስ ተብሎ የሚሰጥ ሳይሆን ከእነዚህ ከላይ ከተመለከቱት ለዜጎች የተሰጡ መብቶች የሚቀዳ መሆኑ በደማቁ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የፕሬስ ነጻነት አቀንቃኝ ነን የሚሉትና ከጀርባ ሌላ ፈንጂ ያጠመዱት ኃይሎች የፕሬስ ነጻነት ተደፍጥጧል ቢሉም ለዜጎች መብት መረጋገጥና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ ሲባል ህገመንግስቱ ለፕሬስ ነጻነት ዋስትና ሰጥቶ መንግስትም፣ ምንም እንኳ መርሁና ተፈጥሮውም ቢሆን፤ ባይፈልግም እንኳ መጣስ እንደማይችል ተገንዝቦ በተግባር እያረጋገጠ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ ይህንን የሚደፈጥጥ ጉድጓድ ውስጥ መግባት ተገቢ ያልሆነ ምግባር በመሆኑም ህገ መንግስቱ ለፕሬስ ነጻነት ልዩ ጥበቃ አድርጓል፡፡ ያለመታደል ሆኖ ግን በሀገራችን የበቀለው የግል ሚዲያ ይህንን ነጻነት ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ የህብረተሰቡን የመረጃ ፍላጎት ማርካትና በህብረተሰቡ ውስጥ የተጋ የመረጃ ልውውጥ እንዳይደረግ የሚሰራ እና ይልቁንም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ስራ በይበልጥ እየሰራ የሚገኝ መሆኑም ሊያስተባብሉት የማይቻል ሃቅ መሆኑን ከቅኝታችን በሚገባ ተገንዝበናል፡፡

ህገ መንግስቱን የጻፈው የሚተረጉመው እንደሆነ በመናገር ስለ ፕሬስ ነጻነት መብት መደፍጠጥ በምክንያትነት ቢቀርብም የሀገሪቱ ሉዓላዊ አካል የሆኑት ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተወከሉበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣን ቢሆን በፍርድ ቤት አንድና ሁለት ዳኛ ከሚተረጉሙት የተሻለ እና በመርህም ለሌላ ሞዴል ሊሆን እንጂ የሚጥላላ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

የግል ሬዲዮንና ቴሌቭዥንን በተመለከተ ጉዳዩ የመሰረተ ልማት (infrastructure) እና ነባሩን የአናሎግ ሲስተም በዲጂታል በመለወጥ ሂደት ነባሩን አናሎግ ለግሉ ዘርፍ ጥቅም ላይ እንደዲውል ቢደረግ ኪሳራ ከመሆኑ ጋር የተያያዘና ከሌላው ልማት ጋር የማጣጣም ጉዳይ እንጂ አፈና ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ ህገ መንግስቱ ውስጥ ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት የሰፈረው ቃል ብቻ እንዲሆን ተፈልጎ ሳይሆን ትርጉም ያለውና በመራራ ትግል የተገኘው ሥርዓት ካለዚህ ነጻነት መጽናት እንደማይችል በመገንዘብ መሆኑም ለታወቅ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ አርሶአደሮች የመሬት ባለቤት ያልሆኑበትን ሥርዓት ከዚህ ሥርዓት ጋር አወዳድሮ ሙግት መግጠም ያንኑ ባላባታዊ ሥርዓት ከመናፈቅ የዘለለ መነሻ የሌለው ሲሆን በታሪካችን በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የተሻለው ዘመን ይህ እንደሆነና ይህን መካድ የታሪክም ሆነ የእውነት መሰረት የሌለው እንደሆነም ሌላው ሊሰመርበት የሚገባውና አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ፡፡ እዚህ ላይ ልዩነት ከመጣ ደግሞ በጸሀይ መግቢያና መውጪያ ላይ ተለያየን ማለት መሆኑንም ህዝቡ በሚገባ ሊያጤነው ይገባል፡፡

ህግን ማስከበርና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መጠበቅ ለመንግስት ስራው ነው፡፡ ለኛ ደግሞ የዜግነት ግዴታና ባልተፃፈ ደብዳቤ የተሰጠ ኃላፊነት ነው፡፡ ዜጎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት አውጥተው ባፀደቁትና ስራ ላይ ባዋሉት ህግጋቶችና ድንጋጌዎች የመጠቀም፣ የመዳኘት፣ የመጠየቅ መብት ያለው እኛው በወኪሎቻችን አማካኝነት ኃላፊነት የሰጠነው ተቋም መሆኑም እውን ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ፕሬሱን በተመለከተ እና የተቃውሞውን ጎራ በተመለከተ ለገበያ አክራሪነት የሚተጉ እና የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማትን ታፔላ የለጠፉ ድርጅቶች ባለቤት ለመሆን ሲጥሩ ማየት በተለይ ከከሸፈው የምርጫ 97 የቀለም አብዮት በኃላ እየተዘወተረ ያለ የእለት ተገባር ነው፡፡ በእነዚህ አለም አቀፍ የሙብት ተሟጋቾች ስም ከተቋቋማው እና ለቀለም አብዮት የተመቹ የሙያ ዘርፎችን እና የተቃውሞውን መንደር ለቀለም አብዮት በማዘጋጀት፣ በማሰልጠንና በማብቃት በሚገባ ከሚታወቁት አንዱ የሆነው ‹‹አለም አቀፍ የጋዜጠኞች ሙብት ተሟጋች ነኝ›› የሚለው “CPJ” የተሰኘው ድርጅት ነው፡፡

ለዚህ ወጋችን መጠናከሪያነት የተመለከትናቸው የCPJ ጥናቶችና መግለጫዎች ላይ  ሲጀምር ሚዛናዊ አለመሆናቸውን በሚገባ መገንዘብ ችለናል፡፡ አለመሆናቸውን ደግሞ ቢያንስ በሪፖቶቹ ላይ ሁሉ የሚመለከተውን የመንግስት አካል ባለማካተቱ ይገለፃል፡፡ ሁለተኛው ነገር ደግሞ አምደኝነትና ጋዜጠኝነት ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን (ከላይ ከተመለከተው ቅኝታችን ያስታውሷል) በመፅሄት ጋዜጣው ላይ ወግ ፀሀፊ፣ ቀልድ ተራኪ በመሆን የምናውቀውቃቸውን ሳይቀር የመፅሄት/ጋዜጦቹ አዘጋጅ እንደሆኑ አድርጎ በሚበዙ ሪፖርቶቹ ላይ ማመልከቱ የጥናቱን አስቀድሞ መክሸፍ የሚያሳየን ነው፡፡

ስለጋዜጠኞች ሙብት ልሟገት፣ ጠበቃ ልሆን የተቋቋምኩ ነኝ የሚል አንድ ተቋም መሟገቻ ሲያጣና ማስረጃ ሲያጥረው የእርሱም ገመና ከመውጣቱና ከመጋለጡ አስቀድሞ ገመናውን የተሸከሙትን ማውጣቱ ሳያንስ፤ መልሶ የስደት  ክስ ማሰማቱ በእርግጥም ተቋሙና መሰሎቹ የቆሙት ስለሙብት ሳይሆን ስኮላር ሺፕ ስለሚፈልጉና ከእነርሱ ፖሊሲ ባሻገር የራሳቸውን በራሳቸው አግባብ የሚያራምዱ ሀገራትን ማተራመስና ስርዓቱን በኃይል ለመቀየር መሆኑን በሚገባ ያረጋገጠልን ሌላውና ሊሰመርበት የሚገባውና ከቅኝታችን የተገነዘብነው ክስተት ነው፡፡

ከላይ በተመለከቱት እና በ10 አመታት የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ወጋችን ማሳያ ሆነው ከቀረቡት አስረጅዎች አንፃር ባለድርሻዎቹን ስናሳርግ ኢህአዴግ /ወይም ገዢው ፓርቲ የብዙሃን ፓርቲን በህገ-መንግስቱ እውቅና ከመስጠት በዘለለ የመድብለ ፓርቲን ሊደግፍ የሚችል ማህበረሠብ መፍጠርና ለሂደቱ መጠናከር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ሲገባው

በተቃራኒው ከእርሱ የተለየ አመለካከት ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች አገር አፍራሾች አድርጎ በመክሠስ የሚያራምደው ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አቋም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለብዙሃን ፓርቲ ስርዓት መዳከምና ከራሱ ከገዢው ፓርቲ ሌላ ጠንካራ ፓርቲ ላለመፈጠሩ አንዱና ዋነኛው እንቅፋት ነው በሚል ላሳለፍናቸው 10 አመታት ሲቀርብ የነበረው እና በመቅረብ ላይ የሚገኘው መከራከሪያ ውሃ የማያነሳ ከመሆኑም በላይ አንዳች ወደ እውነት የተጠጋ ፍሬ ሃሳብ የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፤ ይልቁንም ክሱ በተገላቢጦሽ ከሳሾቹ የሚገለጹበት መሆኑ የሚያጠያይቅ ሆኖ መገኘቱ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ ከእርሱ የተለየ ሃሳብ ስለምናራምድ ብቻ ያለፉ ስርዓቶች ናፋቂዎች የሚል አመክንዮ የሌለው ጥቅል ፍረጃ ውስጥ ገብቶም ያምሥናል ሲሉ የሚከራከሩት ተቃራኒ ወገኖች ፍረጃው ከላይ በተመለከተው አግባብ ከአመክንዮም አልፎ በመሬት ላይ ባለው ነገር የተረጋገጠና ሁነኛ በሆነው ሃገርኛ ብሂልም የተደመደመ መሆኑም በሁለተኛነት ሊሠመርበት የሚገባው ማሳረጊያ ይሆናል፡፡ ማሳረጊያችንን የምናሠልሠው ደግሞ ሁሉንም ሳይሆን ግን ደግሞ በርካታ ተቃዋሚዎችን በተመለከተው እና ከላይ የሚታዩ አስረጅዎችና ሃገርኛ ብሂሎች የተጠቀለሉ መዘርዝሮች ታሳቢ ባደረገው ጉዳይ ነው፡፡ በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያራምዱት አቋምና የሚከተሏቸው መንገዶች ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ አወንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል ሳይሆን በተቃራኒው መሆኑን በሚገባ ማጠየቃችን አያጠራጥርም፡፡ አብዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገና ካፈጣጠራቸው ችግር ያለባቸው በመሆኑ መጀመሪያ ነገር ዴሞክራሲያዊ አስተሳሠብ በውስጣቸው ያልሠረጸ መሆኑን፤ የራሳቸውን የውስጥ ችግር ሳይፈቱ፣ የመቻቻልና እውቅና የመሠጣጣትን ባህል ሳያውቁበትና እያወቁም ሳያደርጉት፣ ከላይ በተመለከተው አግባብና በአንፃራዊ መልኩ የገዘፈ ችግር የሌለውን ገዢ ፓርቲ ቢኖርበት እንኳ የእርሱ ችግር ተቃዋሚዎቹን ዴሞክራቶች የሚያሠኝ አመክንዮ አለመኖሩን አውቀው በመዘንጋት በዚህ ግትር አቋማቸው በወጋችን ለተመለከቱት 10 ዓመታቶች የሄዱበት መንገድ ሁሉ እራሳቸውን የበለጠ ችግር ውስጥ ከመክተት ባሻገር በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ላይም ሆነ ህዝቡ ላይ ያሳየው አንዳች ተጨባጭ ለውጥ እንደሌለ እንኳንስ እኛ የዚህ ዘመን ተጋሪዎች የኢትዮጵያን 10 አመታት ፓለቲካ የተከታተለ ማንኛውም የውጭ አካል የሚቀበለው ተጨባጭ ሃቅ መሆኑንም አጽንኦት ልንሠጠው የሚገባው አጀንዳ መሆኑ የማያጠያይቅ ሆኗል፡፡

የማያጠያይቀውና ሠለስተኛው ተቃዋሚዎችን የተመለከተ ማሳረጊያ ይህ ከላይ የገለፅነው ብቻ አይደለም፤ የ10 ዓመታት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸው ከላይ በሚገባ የተመለከትንላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዋነኛ ችግር የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግሮች ከመፍታትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ከመገንባት ይልቅ ገዢው ፓርቲን በጭፍን ለመቃወምና ከተቻለም ለመበቀል ብቻ የሚያደርጉት ሽኩቻም ሠልስተኛው ማሳረጊያ ሆኖ ሊወሠድ የሚገባይ ይሆናል፡፡ እኚህና ስርዓቱ በፈጠረላቸው እነርሱ ግን በሚክዱት እድል ተጠቅመው የተደራጁቱ ፓርቲዎችም ሆኑ ፕሬሶች ለአንድ ሃገር የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ብሄራዊ መግባባት፣ መቻቻልና በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አብሮ መስራት የምርጫና የፍላጐት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ መሆኑንም መገንዘብ ሲገባቸው መስመራቸውን ስተው ጥያቄያቸውና ትግላቸው የነፃ አውጭነት መሆኑም በሚገባ ከላይ ተመልክቷልና ለቀጣዩ ሂደት የህዝቡ ስንቅና ትጥቅ ሆኖ ሊወሠድ የሚገባውና ከሶስተኛው ጋር ተያያዥ የሆነ ማሳረጊያ ነው፡፡ በዚህና ከላይ በተመለከተው ለሶስተኛው ማሳረጊያ የሚገለጹቱ ፓርቲዎች ከራሳቸው አልፈው ገዢ ስርዓቱንም ሆነ ሃገርን በሚጐዳው ድርጊታቸው ብቻ ተወስነው የሚያበቁ መስሏችሁም እንዳትታለሉ፡፡ ከላይ በተመለከቱት አስረጅዎች እንዳሄስነው በ10 አመታት የፖለቲካ ባህላችን ከተለመደውና ከተመለከትነው በጭፍን የመደገፍና የመቃወም ጤናማ ያልሆነ ፖለቲካ ወጥተው ፖለቲካን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማራመድ የሚያስችል ስልት ነድፎ የሚንቀሳቀሠውን አንድ ፓርቲ (ኢዴፓ) መደገፍና ማበረታታት ሲገባቸው (እንደሚያወሩት እና አለን እንደሚሉት ፕሮግራም) ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ

እውቅና ላለመስጠትና ከተቻለም ለማጥፋት የሚያደርጉትና ህዝብን የሚያደናግር አሉባልታና መሠረተ ቢስ ዘመቻ ስናስተውል ደግሞ ምን ያህል ችግር ውስጥ መሆናቸውንም ሆነ ለማንም የማይጠቅሙ ስለመሆናቸው በአግባቡ ተረድተን የምርጫ 2007 ቅኝታችንንም ሆነ የቅስቀሳ ዘመቻቸውን በዚህ አግባብ ልናጤን የሚገባን ስንቅና ትጥቅ የሚሆነን ማሳረጊያ ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ማሳረጊያ የሚሆነን ደግሞ ምንም እንኳን አሁን የመለወጥ አዝማሚያ ቢኖረውም ከ10 አመታቱ ወጋችን ላይ የተመለከትነው እና ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ መሠረት ለመጣል ከሚያስችሉ መንገዶች ተቃራኒ ለብሄራዊ መግባባት፣ መቻቻልና መደማመጥ አስተዋጽኦ በሌላቸው ከስሜትና ከግል ጥቅም አንፃር ብቻ የሚንቀሳቀሠው ከፍተኛ ቁጥር ያለው የህብረተሠቡ አካል ነው፡፡ በተለይም ይህን ማሳረጊያ ከላይ ከተመለከትነው የ10 አመታት ቅኝታችን ወጣ ብለን የ10 አመታቱ ጉዞ መጀመሪያ ከነበረው ምርጫ 97 አኳያ መመልከቱ ተገቢና ባለድርሻ የሆነውን ህዝብ ግንዛቤ ለመጨመር የሚያግዝ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በዚያ ወቅት ህዝቡ በቅድመ ምርጫውና በምርጫው እለት ያሳየው ተሳትፎ የሚበረታታትና የሚደነቅ የነበረ ቢሆንም በድህረ ምርጫው በተፈጠሩት ምስቅልቅሎች እራሳቸውን እንደ ተቋም በሚቆጥሩ እና ያለቦታቸው ሠላማዊ ትግሉን በተቀላቀሉ (ከላይ በሚገባ በሃገርኛ ብሂላችን ያወሳናቸው) የግራ ዘመም አስተሳሠብ በተጠናወታቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና የግል መስለው የፓርቲ ልሳናት በሆኑ ፕሬሶች ተታሎ በስንት ጥረት የተገኘው ውጤት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ መቸለሱ ሊሠመርበት የሚገባውና ሊደገም የማይገባው መሆኑ አጽንኦት ሊሠጠው የሚገባውና ህብረተሠቡን የተመለከተ ማሳረጊያችን ነው፡፡ ከ10 አመታት ወጋችን ያየነውና በሃገርኛብሂላችን ያጠናከርነው ሌላውና ዋነኛ ባለድርሻ የሆነውን ህብረተሠብ የተመለከተው፤ በተለይም ከምርጫ 2007 አኳያ ልብ ሊባል የሚገባው ማሳረጊያ ደግሞ ይህ ነው፡፡ ትናንት ጀግናና ከእነርሱ ወዲያ ላሳር ብለን ያጨበጨብንላቸው ፓርቲዎች ትግሉን ከገደል ከተው ግማሾቹ ወደለየለት ፀረ-ዴሞክራሲ ካምፕ፣ ገሚሶቹም አገር ጥለው በመሄድ ወደግል ስራቸውና ሌሎቹም አስተሳሠባቸውን ሳይቀይሩ መለያ ቀይረው በአዳዲስ ሰዎች እንደመጡ ህሊናችን እያወቀና በጊዜው ወስነው የነበረው ውሳኔም ለትግሉ የማይጠቅም እንደነበር ከውጤቱም አረጋግጠን ሳለ፤ ለችግሩ የተለዩ አካላትን ተጠያቂ በማድረግ ግትር አስተሳሠባችንን እንደጠቃሚ እሴት አድርገንና ከባህሪያችን ጋር አዋህደን መቀጠላችንን ስለመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታና የግንባታው ትሩፋት አካልነታችን አሽቀንጥረን ልንጥለው የሚገባ፣ ጊዜ ያለፈበት ኋላ ቀር አስተሳሠብ መሆኑን የተመለከተው ነው፡፡

ይህን፣ በሶስት ክፍል የተመለከትነውን የሶስት ምርጫዎች ወግ የምናጠቃልለው በክፍል አንድ ትርክታችን እና ወጋችን መግቢያ ላይ ለተመለከቱት እና ታንሠላስሉት ዘንድ ለቀረቡ ሃገርኛ ብሂሎች የምርጫ 2007 ቅኝታችንን እናስተካክልበት ዘንዳ መገለጫ የሆኑ ፖርቲዎችን በማቅረብ ነው፡፡

"ሲሸጡልን ቀርቶ ሲያስማሙን እናውቃለን" ህዝቡ፣ "ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል በዳሮ" አንድነት፣ "ስደት ለወሬ ይመቻል" ግንቦት 7፣ "ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ" አንድነትና ሰማያዊ፣ "ቂቤና ድልህ" ኢህአዴግ፣ "አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል" መድረክ፣ "አማትና ምራት ሳይግባቡ መሬት" መድረክና አንድነት እንዲሁም መኢአድና አንድነት፣ "እንስራ ያለ ጀሮ ያለማንገቻ ከበሮ" ሰማያዊ፣ "ከነቁ እስቃለሁ ካልነቁ እሥርቃለሁ" አንድነት፣ "ከወገብ በላይ ታቦት ከወገብ በታች ጣኦት" መድረክና መኢአድ፣ "ዘጠኝ መርፌ አንድ ማረሻ አይሆንም " የቀድሞው ቅንጅት፣ "የበሠበሠ ዝናብ አይፈራም " ሰማያዊ፣ "የጐባጣ አሽከር አጐንብሶ ይሄዳል" መድረክ፣ "ድመትን በቆሎ መጠርጠር" ምርጫ ቦርድ ፣ "ጥንቸል እንደ አንበሳ እጮኻለሁ ብላ ተሠንጥቃ ሞተች" ሰማያዊ፣ "ጾማ ጾማ በፀሎተ ሃሙስ እርጐ ትልስ" ሰማያዊ፡፡ ቸር እንሰንብት።